## “ለአገራችን ጥቅም መቆም ብቻ ከሆነ በእኛና በኢሕአዴግ መካከል ያለዉ ልዩነት ትንሽና በቀላሉ ሊፈታ የሚችል ነዉ !

*ዶር ያዕቆብ ሃይለማሪያም*



# ግልፅ ደብዳቤ
# ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለክቡራን ዳኞች

## ከዶ/ር ያቆብ ኃ/ማርያም

በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የወንጀል መዝገብ የተከሰስን ሰዎች እጅግ ከባድና ዘግናኝ ክሶች በአቃቤ ሕግ ተመስርቶብናል:: የተከሰስንባቸው መሠረተ ቢስ ክሶችን በመቃወም ተገቢውን ሕጋዊ ክርክር ለማቅረብና መልስ ለመስጠት እውቀቱም ሆነ ተሞክሮ ሣያንሰን፤ በሀገሪቱ ከሚገኙ ምርጥ ጠበቆች ለማቆም ሣያቅተን ክሱን ላለመከላከል መርጠናል::

ይህ ክስ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍ/ቤት የቀረበ ዕለት ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም በመንግሥትና በእኛ በተከሳሾች መሀል ያለው ያለመግባባት በውይይትና በመግባባት ሊፈታ የሚችል ፖለቲካዊ ጥያቄ እንጂ የወንጀል ጉዳይ አለመሆኑን በአፅንኦት አሳስበው ነበር:: በጉዳዩ እስተያየታቸውን የሰጡ ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅትና የአንዳንድ አገር መሪዎችም ጭምር አለመግባባቱ ፖለቲካዊ መሆኑን አሳሳበው በውይይትና በመግባባት እንዲፈታ በብዙ ተማፅነዋል:: ተከሶሾችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲለቀቁ እነሆ ተማፅኖአቸውን እስከዛሬ አላቋረጡም:: ብዙ ኢትዮጵያዊያንም አለመግባባቱ የወንድማማችና የእህትማማች እንደማሆኑ መጠን የቂምና የቁርሾ ጠባሳ በሚተው በሕግ እሰጣ እገባ ሣይሆን በውይይት መፍትሔ ይሰጠው ዘንድ መንሥትን ለማሳመን ብዙ ጥረዋል:: ኢሕአዴግ ለዚህ ሁሉ አቤቱታ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለቱ እኛም ተከሳሾች እነዚህን ግልፅ የሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች በሕግ ተተብትበው፤ የሕግና የፖለቲካ ጥያቄዎች ልዩነታቸውን ደብዝዞ የኢትዮጵያ ሕዝብን እንዳያሳስት በሚል በፍ/ቤት የቀረበብንን ክስ ላለመከላከል ወሰንን::

እኔም ይህንን በክሱ ላይ ያለኝን የመደምደሚያ ሀሳብ በግልፅ ደብዳቤ ስገልፅ የፍርዱ ሂደት ወደማጠቃለያው በቀረበበት ወቅት አቃቤ ሕጉ ያቀረባቸው ማስረጃ ተብዬዎች ክሱን አያስረዱም፤ በነፃ እንለቀቅ ብዬ የመጨረሻ ተማፅኖዬን ለፍ/ቤቱ ወይም ለሌላ አካል ለማቅረብ አይዳለም:: የተከበረው ፍ/ቤት እንደሚረዳው በወንጀል ክርክር የተከሳሽ የመዝጊያ ንግግር የሕግ አንቀፅና ማስረጃዎችን በመተንተን ብቻ ሣይወሰን፤ ብዙና ሰፋፊ አድማሳትን ሊዳስስ ይችላል::

በአገራችን በተለያዩ ጊዜያት በወቅቱ የነበረውን ስርአት እንለውጣን በማለት በተነሱ አገር ወዳዶች ላይ ክሶች ተመስርተው፤ ትልልቅ ፍርዶች ተበይነዋል:: በእነ በላይ ዘለቀና በጀነራል መንግሥቱ፤ በጀነራል ታደሰ ብሩና በኮ/ል አለሙ ቂጤሣ ላይ የተመሰረቱት መሠረተ ቢስ ክሶችና የተሰጡት ኢፍትሐዊ ፍርዶችን በምሣሌነት መጥቀስ ይቻላል:: ይህ ከፊታችን ያለው ፍርድ ግን በሀገራችን ፍትሕ ላይ ከኢኮኖሚው ተፅዕኖ፤ በአገራችን ሠላም ልማትና ዲሞክራሲ ከማቀጨጭ ወይንም ከማጎልበት አንፃር በጠቅላላው ፍርዱ በአገራችን መፃኢ እድል ላይ ከኢኮኖሚው ጫና ሲታይ ከዚህ ቀደም በአገራችን ከተካሄዱት ክሶችና ፍርዶች ሁሉ የተለየና የላቀ ነው ብል የተሳሳኩ አይመስለኝም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ፍርድ በሚሰጥበት ወቅትም የኢትዮጵያውያንና የመላው አለም ሕዝብ አይንና ቀልብ በዚህች በትንሽ ክተማ በምትገኝ ፍ/ቤት ላይ ያተኮረ እንደሚሆን አልጠራጠርም::

በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ላይ በተመሰረተው ክስ በእውን የተከሰሱት ኢንጂነር ኃይሁ ሻውል ወይንም የአለም የሰብአዊ መብት ተሸላሚ ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም፤ ወይንም ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፤ ወይንም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ወይንም የተቀረነው አይደለንም:: ዛሬ በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ፋይል የተከሰሰው ፍትሕ ነው:: ዛሬ ለፍርድ የሚቀርበው ራሱ ዲሞክራሲ ነው:: ዛሬ ቢፈረድብንና ለእስራትና ለሞት ብንዳረግ የሚሞተው ሠላም ነው:: ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕግ ክቡርነት ላይ ያለው እምነት ነው::

በዚህ በተከሰስንበት ጉዳይ የተከበረው ፍ/ቤት ትልቅ ፈተና ቀርቦለታል:: በዚህ ፍርድ አማካኝነት ፍትሕ ያሸንፋል ወይም ግፍ! በደልና ጥላቻ በአገራች ይነግሣል:: በዚህ ፍርድ ዲሞክራሲ የበላይነቱን ይይዛል! ወይንም እምባገነንነት ይንሰራፋል:: በዚህ ፍርድ ሠላም ይመሰረታል ወይንም ምናልባት የመበጣበጥና የመናቆር ዘር ይዘራል::

እኛ ተከሳሾች መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚያውቀው ፍትሕ ተነፍጉት የኖረው ሕዝባችን ከፍትሕ እንዲቃመስ! የፖለቲካ ነፃነት ቀምሶ የማያውቀው ሕዝባችን ከነፃነት እንዲቋደስ ለዘመናት ሠላም ያጣው ሕዝባችን ሠላምን እንዲያጣጥም ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ተላቆ ክብር ያለው ኑሮ እንዲኖር ለማስቻል የበኩላችንን አስተዋፅኦ ከማድረግ ሌላ ምንም አላማ የለንም:: በሀገራችን ለፍትሕ መሟገት! ለሠላም መቆም ለነፃነት መታገል በእስርና በሞት የሚያስቀጣ ከሆነ እንደ ክሱ ጥፋተኞች ነን ሞትንም ሆነ እስራትን በፀጋ እንቀበላለን:: እስትንፋሳችን እስካለች ድረስ ግን ለሕዝባችን ፍትሕ ከመሟገት! ለአገራችን ለሠላም ከመስራት! ለዲሞክራስ ከመታገል! ለአገራችን አንድነት ከመጣር ለአንድ ቀንም ሲሆን አንዘነጋም:: እኛ በአገር ክህደት ወንጀል ጥፋተኞች የምንሆንና ሊፈረድብንም የሚገባው የራሳችን የግል ጥቅም ከአገራችን ጥቅም ያስቀደምን ዕለት ወይንም ለሕዝባችን የገባነውን ቃል ያጠፍን እለት ነው:: እንዲህ አይነት «ወንጀል» በፈፀምን ጊዜ ይቅርታ አንጠይቅም! ይቅርታ እንዲደረግልንም አይገባም::

ለመሆኑ በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ፋይል ከተሰን ስማችን የዘረዘረው እነ ማን ነን::

በቅንጅት ዙሪያ የተከሰስነውና ዛሬ በተከሳሽነት የቀረብነው ግለሰቦች በተለይም አዛውንቶቹ ፓርቲ ውስጥ የገባነው በአፍሪካ በሰፊው እንደሚደረገው ስልጣንን ተገን አድርገን ገንዘብንና ሌሎች የግል ጥቅማችንን ለማሳደድ አልነበረም:: እንደእውነቱ ከሆነ ብዘዎቻችን ለኑሮአችን በቂ ገንዘብ ያለን ነን:: የሥልጣን ፍላጉትም አልነበረንም:: ፓርቲው ውስጥ የሥልጣን ፍላጉትም አልነበረም ፓርቲው ውስጥ ያስገባን:: በነበርንባቸው የሥራ መስኮች ይብዛም ይነስ ሥልጣን የነበረን ግለሰቦች ነን:: እንዲሁም በዚሁ መዝገብ የተዘረዘሩት ወጣቶች ለድካማቸው ምንም ካሣ ሳይፈልጉ የወጣትነት የጨዋታ ጊዜአቸውና እፍላ ጉልበታቸው ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ምፅዋት ያቀረቡ የነገ የአገር ተረካቢ አለኝታዎች ናቸው:: ከእኛው ጋር ታስረው የሚገኙት ወጣት ጋዜጠኞች የሕዝባችንን የንግግርና የጹሁፍ ነፃነት በብዙ እርምጃዎች ወደፊት ያራመዱ የዲሞክራሲ አርገበኞች ናቸው::

ጀነራል መንግሥቱ ንዋይ የእነ ኃ/ሥላሴ መንግሥት አስወግደው ስርአቱን ለመለወጥ የነበራቸው እራዕይ ሳይሳካ ቀርቶ በአገር ክህደት ወንጀል ተከሰው ፍ/ቤት ቀርበው የተናገሩት ለእኛም አግባብነት አለው:: ጀነራሉ ለምን የኃይሌን መንግሥት ለማስወገድ እንደፈለጉ ምንስ ጉድለታቸው ነው ብለው በተጠየቁ ጊዜ የሰጡት መልስ እንዲህ የሚል ነበር «እኔ ብፈልግ በየቀኑ መኪና መቀያየር እችል ነበር ብፈልግም ምርጥ የአውሮፓ ሻምፓኝ ልጉነጭ እቅሙ ነበረኝ ሰው ቤተመንግሥት ለመግባት ስኮለኮል እኔ ከልካይ አልነበረብኝ ይህንን ሁሉ ይቅርብኝ ብዬ አገሬን ከአለችበት ድቅድቅ ጨለማና ውርደት ለማውጣት ነበር የተነሳሁት» ዛሬ አንዳንድ የቅንጅት መሪዎች ይህንኑ የጀነራል መንግሥቱን ቃል በዚሁ ችሎት ይደግሙት ነበር:: በእኛና በእነ ጀነራል መንግሥት ካሉ ብዙ ልዩነቶች ዋነኛው የትግል ስልት ሆኖ እኛ የመንግሥት ለውጥ በሕዝብ ምርጫ ይሁን ስልንል እነ ጀነራል በሀይል ነበር ለውጥ ለማምጣት የመረጡት:: በቅንጅት መሪዎችና አባላቱ ቁም ነገር ያለው የሕይወት አላማና ግብ መለኪያው የሚጠጣው ሻምፓኝ ወይንም የሚቀርጠው ሙማ ወይንም የሚነዳው መኪና ወይንም የሚኖርበት ቪላ አይደለም:: ዛሬ በዚህ ፋይል ተከሰን በእስር ቤት የምንገኝ ዜጉች ሁሉ ፍላጉትና አላማ ከሌሎች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር በመሆን የዛሬዎቹን አሳሪዎቻችንን ጭምር ቅሌን ጨርቄን ሣንል ለምንከፍለው መስዋዕትነት ምንም ዋጋ ሣንሻ ለአንዴና ለሁሌም ታሪካዊና ተወዳጅዋ አገራችንን የሸፋፈናትን የድህነት ማቅ ለመግፈፍና የዲሞክራሲ ጥማትዋንም ለማርካት ነው:: የዓላማችን መጀመሪያና መጨረሻ የሕይወታችን ሕልውና ምክንያት ይሕና ይህ ብቻ ነው:: የሰው ሕይወት አጭር ነች በተለይም አዛውንቶቹ ከሰው ሕይወት መደምደሚያ ሩቅ እንዳልሆንን

እንገነዘባለን ይህ ፍፃሜ ከመድረሱ በፊት ግን አገራችን አሁን ከምትገኝበት የውርደት አዘቅት አውጥተን በዲሞክራሲና በልማት ጉዳና መራመድ የጀመረች አገር ለልጆቻችን አውርሰን ልናልፍ እንፈልጋለን።

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ዳኞች ተከሳሾች በሙሉ በደም የራሰውን የአገራችንን የፖለቲካ ታሪክና የተከፈለውን መስዋዕትነት ጠንቅቀን እናውቃለን። ምናልባትም እኛም እራሳችን ለዚሁ ታሪክ ሰለባ ልንሆን እንደምንችል እንገነዘባለን።

የኢትዮጵያ መሪዎች አጼ ዮሐንስ፤ አጼ ቴዎድሮስ፤ ልጅ እያሱ፤ ንግሥት ዘውዲቱ፤ አጼ ኃይለሥላሴ፤ ክቡር አቶ አክሊሉ ኃብተወልድ፤ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን፤ ጄነራል አማን አንዶም፤ ጄነራል ተፈሪ በንቲ እንዳቸውን በሥልጣን ላይ እያሉ በአልጋቸው በሠላም ሕይወታቸው አልፎ ዘመድ ወዳጅ ተሳቅሶ አልቀበራቸውም። የአጼ ምኒሊክ አሟሟት በጥያቄ ውስጥ ያለ ነው። የኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም እጣ ፈንታ በውል አይታወቅም። እዚህ ላይ ሊባል የተፈለገው በኢትዮጵያ ውስጥ በመሪነት መቀመጥ ምን ያህል አደገኛ መሆኑን ለማመልከት ነው። እንግዲህ የአገራችን የፖለቲካ ሂደት አደገኛ መሆኑንና በደም መሰወሱን እያወቅን ነው የዛሬዎቹ እስረኞች ተከሳሾች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እጅን ማስገባት ምን ያህል አደገኛ መሆኑን እየተረዳን የእሣት ራት ሊያደርገን የሚችል ጉዳና ለምን መረጥን፤

ሀ. መሪዎች ከግል ጥቅም ጥልቅ የአገርና የሕዝብን ጥቅም አስቀድመው ሕዝብን አሣታፊ የሆነ ራዕይ ሰንቀው የመንዝ ልምድ በአገራችን እንዲሰርፅ ነው፤

ለ. አሸናፊው ወደ ቤተመንግሥት ተሸናፊው ሰሞት ለእስራትና ለስደት የሚዳረጉበት የአገራችን የሥልጣን ሽግግር የታሪክ ሽክርክሪትን ሰብረን ሥልጣን በጠመንጃ ሣይሆን በምርጫ ሣጥን የማመነጭበትን ሒደት ለመፍጠር ነበር፤

ሐ. ኢትዮጵያዊ ሕፃን ማሙሽ ስጋው ስጋውን በልቶት በአጥንቱ ቀርቶ ምስሉ በአለም ዙሪያ በቴሌቪዥን መስኮት ሲያንቆራጥጡት ማየት ስላሳፈረን ይህንን አሳፋሪ ሁኔታ ለመለወጥ ሕልም ስለነበረን ነው፤

መ. በተለያዩ ጊዜያት በስራም ሆነ በሌሎች በተለያዩ አጋጣሚዎች በውጭ አገር የምናገኛቸው ባዕዳን የሚጠይቁን ስለገናናው ታሪካችን ወይም ስለ ዝነኛ አትሌቶቻችን ሣይሆን ዘንድሮ በአገራችሁ ስንት ሰው በችጋር ያልቃል? የሚለው ውትወታቸው ስላስቆጨን ነው።

ሠ. በመካከለኛው ምሥራቅና በሌሎችም አገሮች ከባሪያ ባልተሻለ ደረጃ የሚዋረዱት እህቶቻችን፤ ወንድሞቻችንና ልጆቻችን በአገራቸው ተምረው ቤተሰብ አፍርተው ከብረውና ከብደው በአገራቸው የሚያስኖራቸው ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

ረ. ወጣቱ በአገሩ ተስፋ ቆርጦ ከአገሬ የባሰ ሌላ አገር አይኖርም ከአገሬ ውጥቼ ቢሻው ሲኦል ልግባ በማለት ከአገሩ የሚሸሸው ወጣት በአገሬ ያልፍልኛል የሚለው ተስፋ የሚሰንቅና የወጣውን ወደ አገሩ እንዲመለስ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ነው።

ሰ. በአንድ ወቅት በኢንተርኔት ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሀፍረትና ውደርደት ናት ተብሎ በአንድ አፍሪንካዊ የተፃፈውና በመላው አለም የተነበበውን በመቀየር ኢትዮጵያ የአፍሪካ መኩሪያ ነች መባል አለባት ከሚል ተነሳስተን ነው

ሸ. በቀይ ሽብር ጊዜ በጉራጌ ዞን በቸሀ ወረዳ በጉብርያ ት/ቤት አንድ እናት በተገደለው ልጇ ሬሳ ላይ ሕዝብ እንዲረጋገጥበት ሆኖ የልጇ ጭንቅላት ተቆርጦ ያንን የልጅ ጭንቅላት ሠርቃ በጉያዋ ሸጉጣ ስትሮጥ ያየነው ከሕሊናችን አልጠፋ ስላለንና እንዲህ አይነት ነገር በአገራችን እንዳይደገም በማሰብ ነው።

ቀ. አገራችን በአንድ ጀምበር ጠፍታ ብታድር የሚደሰቱና ለምኞታቸውም ስኬት ዝግጅት የሚያደርጉ ጠላቶች እንዳለብን ተረድተን እራሳችንን አጠናክረን የማንም ተገቢ ጥቅም ሣንነካ የእኛንም ሣናስነካ ጠንካራና በራሷ የምትተማመንን፤ ሲሆን ለዓለም ሰላም ተገቢውን ድርሻዋን የምታበረክት ኢትዮጵያን ለመገንባት ነው።

በሕዝብ ፍቃድ ሣይሆን በጦር መሣሪያ ኃይል ሥልጣን ላይ የወጣ አንድ ቡድን በምርጫም ይሁን በኃይል ከሥልጣን ሳውርድህ የሚለውን ተቀናቃኝ በአገር ክህደት ወንጀል መክሰስ ሶሶተኛው አለም በተለይም በአፍሪካ የተለመደ ነገር ሆኗል። በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የአገር ክህደት ክሶች ተደጋግመው ታይተዋል። ስለዚህ በእኛ ላይ የተመሰረተው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል በማፍረስ የሚለው የፈጠራ ክስ

አሳዛኝ ከመሆኑም ሌላ በእኛ ላይ የተጀመረ አዲስ ነገር ባለመሆኑ እንደ ተከሳሽነቴ በበኩሌ በቁም አልቆጠርኩትም። እኔን እንደውስጥ እግር እሳት የለበለበኝ በአገሬቱ የፍትሕ ሥርዓት ላይ የነበረኝ እምነት ከመሰረቱ ያናጋውና ልቤን ያቆሰለኝ በዘር ማጥፋት ወንጀል መከሰሳችን ነው። ለመሆኑ የማንን ዘር ልናጠፋ ነው? ዘወትር የውጪ ወረራ ገፈት ቀማሽ የሆነው እጅግ የምንወደውና የምናከብረው የሰሜኑ ሕዝባችንን ነው? እውነቱን እንነጋገርና አጥንት እንቆጣጠር ከተባለ ለአንዳንዶቻችን በዘር ማጥፋቱ እልቂት ልጆቻችንን መጨመር ይኖርብናል ማለት ነው። እውነቱን እንነጋገር ቁጣዬንና ንዴትን በአግባቡ ሊገልፁ የሚችሉ አማርኛም ይሁን እንግሊዘኛ ቃላት የሉም። እንደዚሁም የሚያናድደኝን የዘር ማጥፋት ወንጀል ምን እንደሆነ በፅሁፍ ሣይሆን በአካል ስላየሁት ነው።

ከቡራን የኢትዮጵያ ሕዝብና ዳኞች በሩዋንዳ የቱትሲን ዘር የማጥፋት ወንጀል ተጠርጣሪዎችን ለመዳኘት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተቋቋመው አለም አቀፍ ፍ/ቤት በአቃቤ ሕግነት በምሰራበት ወቅት የዘር ማጥፋት ወንጀል ምን እንደሆነ በሕግሩ ቆሞ ሲሔድ አይቻለሁ! በጣም ጥቂቶቹን ልጥቀስ፡-

- በአንድ ቀበሌ የቱትሲ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ እናቶች ልጆቻቸውን ወደ አንድ የስብሰባ ቦታ እንዲያመጡ ታዘዙ ከዚያም እናቶቹ ትላልቅ ጉድጓዶች እንዲቆፍሩ ተነገራቸው። ጉድጓዱን ቆፍረው ሲጨርሱ እያንዳንዷ እናት ልጇን ከዚያ ጉድጓድ ውስጥ እንድትወረውር ተገደደች። ከዚያም ልጆቹን አፈር አልብሱ ተባሉ ሲያለብሷቸው ልጆቹ እማዬ አውጪኝ እያሉ ከጉድጓድ ለመውጣት ሲሿጥጡ እናቶቻቸው በላያቸው አፈር እንዲያለብሷቸው ተገደዱ. ከጉድጓድ ውስጥ የሚወጣው ሰቅጣጭ ድምፅ ፀጥ ሲል ነበር እናቶቹ እራሳቸውን ስተው የወደቁት። እናቶች ይህን ያደረጉት የተቀሩትን ልጆቻቸውን ከሞት ለማዳን ነበር።
- ከ25ሺህ በላይ የሚሆኑ ቱትሲዎች እናንተ ኢትዮጵያውያን ናችሁ ሒዱ ወደ ሀገራችሁ ግቡ ተብለው እጃቸው የፊጢኝ ታስረው ወደ ሰሜን አቅጣጫ በሚፈስ ወንዝ ውስጥ ተወርውረው ሰውነታቸው ፍፁም ነጥቶ የተነሳውን ቪዲዮ ለዐቃቤ ሕግ ማስረጃነት አቅርቤዋለሁ። ያም ወንዝ በፌዝ ለጊዜውም ቢሆን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተባለ።
- በአንድ ሙራቢ በሚባል ቀበሌ ከ3ሺ የሚበልጡ ቱትሲ ወንዶች፤ ሴቶችና ሕፃናት ግንባራቸው በቆንጨራ ተበርቅሶ ወደ ሬሳ ማጨቂያነት በተቀየረ ት/ቤት በሰው ልጅ ማፈሪያነት ለታሪክ ተቀምጧል።
- በጠቅላላው በሩዋንዳ በ90 ቀናት ውስጥ ወደ 1ሚሊዮን የሚጠጉ ቱትሲ አዛውንትና ሕፃናት በቆንጨራ ተጨፍጭፈዋል። ጥቂቶች የታደሉት ደግሞ የሚገደሉበትን ጥይት እንዲገዙ ተደርገዋል።
- በሌላ አህጉር ማለትም በእስያ 2 ሚሊዮን ካንቸንቺያኖች በዘርና በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ተጨፍጭፈዋል።
- እንዲሁም በሒትለር በጀርመን 6 ሚሊዮን አይሁዶች በዘራቸውና በሀይማኖት ምክንያት ተጨፍጭፈዋል።

ከሚሊዮን የማያንሱ አርመኖች በቱርኮች ተጨፍጭፈዋል።

እኛ ደግሞ በዘር ማጥፋት ወንጀል የተከሰስነው ከእኛ ጋ ምንም ግንኙነት በሌለው፤ ሕዝቡ ድምፁ ይከበር ብሎ በተነሳሳበት ወቅት አንድ ቤት በከፊል በመቃጠሉና ጥቂት ተመሳሳይ ጉዳይ በአንዱ ብሔረሰባችን ላይ ደረሰ የተባሉት ጉዳትም ቢሆን በዚያ ብሔረሰባችን አባልነታችሁ ሣይሆን ለኢሕአዴግ ካድሬና ባለሥልጣናት ሆነው ባደረሱት በደል ነው የሚል ግምት አለን። ሕዝባችን አቃቤ ሕጉ ከሚገምተው በላይ ብልህና ጨዋ ነው። በቅርብ ጊዜ በፖለቲን ቡድኖች ቀስቃሽነት ከተደረጉ ጥቂት የብሔረሰቦች ግጭት ሌላ ሕዝባችን በራሱ ተነሳስቶ በዘርና በሃይማኖት ልዩነት የተጋጨበት ወቅት በታሪክ የለም።

## ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ

ዐቃቤ ሕጉ በእኛ በተከሳሾች ላይ ክስ መስርቶ የዋስ መብት እንድንከለከል ፍ/ቤቱን በአሳሰብንበት ወቅት የሃገር ክህደት ወንጀል ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል መሆኑን ገልጾ ነበር። ሆኖም ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ የወንጀሎች ቁንጮ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንጂ የሃገር ክህደት ወንጀል አይደለም። ፈረንጆች ( the most heineous, the most egregious) ወንጀል ይሉታል። አዶልፍ ሂትለር የይሁዶች ዘርና ሃይማኖት ከምድረ ገጽ ለማጥፋት 6 ሚሊዮኖችን በፈጀበት ጊዜ በወቅቱ ወንጀሉን የሚገልጽ ቃል ስላልነበረ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚንስትር የነበሩት ዊንስተን ቸርችል ʺስም የለሽʺ ወንጀል( namless crime) ብለውት ነበር። ይህ አንድን ዘር ወይም ሃይማኖት የሚያጠፋ ወንጀል ምን ተብሎ ይጠራ ብለው ምሁራን ሲመረምሩ ለምፓኪን የተባለ ከአውስትራሊያ ወደ አሜሪካ የተሰደደ አይሁድ እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ቃል ሲፈልግ(geno) በግሪክ ዘር የሚል ቃል፣(cide) በላቲን በጅምላ መግደል የሚሉትን ሁለት ቃላት አጣምሮ (geniocide) በአማርኛ ʺዘር ማጥፋትʺ ብለን የተረጐምነውን ቃል ፈለሰፈ። ይህም ወንጀል በጊዜው ባለመታወቁ ናዚዎች እንኳን በተለያዩ የጦር ወንጀሎች እንጂ በዘር ማጥፋት ወንጀል አልተከሰሱም። እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ዙሪያ በዘር ማጥፋት ሶስት ክሶች ሲመሠረቱ ሁለቱ በኢትዮጵያ በደርግ ባለስልጣናት እና በእኛ ላይ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በሩዋንዳ ነው። በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ የጨፈጨፈው ሳዳም ሁሴን እንኳን ቢሆን የተከሰሰውና የተቀጣው በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሶ ሳይሆን በሰው ልጆች ላይ በፈጸመው በ (crime against humanity) ነው። በሁለቱ መሀከል ደግሞ የጐላ ልዩነት አለ።

የዘር ማጥፋት ወንጀል በጠቅላላው በዓለም ሕዝብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል ነው። አንድ ዘር ወይም ሃይማኖት ሲጠፋ ተጐጂው ጠቅላላው የሰው ልጅ ስለሆነ በዘር ማጥፋት ወንጀል የሚጠረጠር ሰው በማንኛውም ሃገር ክስ ሊቀርብበት ይችላል።

እኛን የሚያስቆጨን በግፍ መታሠራችን አይደለም። የጀመርነው የዲሞክራሲ ሂደት ለጊዜውም ቢሆን ቢስተጓጐልም እኛን ያስቆጨን ስማችን ከዘር ማጥፋት ወንጀል አጠገብ መስፈሩ ነው። በዚህ መሠረተ ቢስ ክስ ዐቃቤ ሕጉ በግማሽ ገድሎናል፣ ስማችንን አጉድፎታል። ሰብዕናችንን ከማራከሱም በላይ በምንወደውና በምናከብረው በሰሜኑ ሕዝባችን ፊት በጠላትነት ሊያስፈርጀን ሞክሮአል። እንዴትስ የሃገራችን ታሪክ እንደሚያጉድፍ አልተረዳውም። አሁን በእውነቱ በጊዜው ነፍሰ ጡር የነበረችው ወ/ሮ ሰርከዓለም ፋሲል ወይም ሰውን ቀና ብላ የማታየውን ሰብለ ታደሠ ወይም የትግራይ

ብሄር ተወላጁ ዳዊት ከበደ የራሱን ዘር ለማጥፋት ሞክሮአል ብሎ ዐቃቤ ሕግ አምኖ ነው! በእነዚህ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ላይ ክስ የተመሠረተው? ወይስ በትህዛዝ?

የሕዝብ መብት ለማስከበር የታደልን የሕግ ባለሙያዎች እኮ ፍፁም እውነተኛነት ፣ለሕግ ፍፁም ታማኝነት ፣ፍፁም ሐቀኛ ሆነን መገኘት ይጠበቅብናል:: ይህ ካልሆነ በሕግ ዕውቀት ለመካን ያደረግነው ረጅም የሕግ ጥናት ዘመናት ባከኑ ማለት ይቻላል:: ለዚህም ነው የሕግ ሥነ ምግባር ትምህርት(sepal ethics)
በሕግ ጥናት ፕሮግራም አጽንኦት የሚሠጠው:: በምንም መልኩ ከተከሳሾች ጋር በአልተያያዘ ምክንያት አንድ ቤት ተቃጥሎ ቢሆን እንኳን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያጉድፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ መመሥረት በአንድ ሚሊዮን ቱትሲዎች በሁለት ሚሊዮን ካምፑችያኖች በአንድ ሚሊዮን ተኩል አርመኖች በ6 ሚሊዮን ይሁዶች ደም እንደመቀለድ ይቆጠራል:: የሕግ ባለሙያዎች ፍትሕን በሹመትና በገንዘብ ቀርቶ በሕይወታቸው እንኳን መቀየር የለብንም:: አለበለዚያ የተከበርን የሕግ ባለሙያዎች ከመሆን ፈንታ አብላጫ ገንዘብ ለከፈለን ገዢ ወይንም ሿሚ ራሳችንን ሸጠናል ማለት ነው::

ከዘር ማጥፋት ወንጀል ከመመሥረት ባልተናነሰ መልኩ ዐቃቤ ሕጉ የክስ አመሠራረትና የማስረጃ አቀራረብ የሚያስት ብቻ ሳይሆን ያሳዝናልም:: ዐቃቤ ሕጉ በየቀጠሮቹ ጭብጦችን በሚያስይዝበት ወቅቶች ተከሳሾቹ አድመኞች፣ በወንጀሉ ተባባሪዎች መሆናቸው በማስረጃ ሳይረጋገጥ በአድመኝነትና በወንጀለኛነት ፈርጆናል:: ስለሆነም በአንዱ ተከሳሽ ላይ የቀረበው ማስረጃ በሁሉም ተከሳሾች ላይ እንደቀረበ ተደርጉ እንዲቆጠርለት ክቡር ፍርድ ቤቱን አሳስቧል:: ይህ ቅያስ ወይም(strategy) ዐቃቤ ሕጉ እራሱ ያመነጨው ሳይሆን የኑረምበርግ ፍርድ ቤትን ካቋቋመው ቻርተር የተገለበጠ ነው:: በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል አድራጊ አገሮች ናዚዎችን የሚዳኙበት ሕግ ቻርተር አወጁ:: በዚህም አዋጅ የናዚ የፓርቲና ሌሎቹም የናዚ ድርጅቶች በሙሉ ሕገ ወጥ ደርጅቶች(criminal organizations) መሆናቸውና የእነዚህም ድርጅቶች አባላት በአባልነታቸው ብቻ ወንጀለኞች እንደሆኑ ደነገጉ:: ስለሆነም በአንዱ የፓርቲ አባል ላይ የቀረበ ማስረጃ በሁሉም የናዚ አባላት ሁሉ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን በቻርተሩ ተደነገገ:: ይህ የቻርተሩ አንቀጽ "ወንጀል የግል ነው" የወንጀል ድንጋጌ ወደ ኋላ ሄዶ ወይንም(retroactively) አይሠራም የሚለውን የወንጀል ሕግ መርህ ወይንም(doctrine) ስለሚጻረር በዓለም የዓለም ሕግ ምሁራን ዘንድ በጽኑ የተነቀፈ ነው:: በምሳሌ ሳስረዳ በዐቃቤ ሕጉ አስተሳሰብ የቅንጅት አመራር አባል ያዕቆብ ኃ/ ማሪያም አባል በመሆኑ

ብቻ ወንጀለኛ ነው ማለት ነው ቀጥሎም በያዕቆብ ላይ የሚቀርበው ማስረጃ ቅንጅትን በሚደግፉ ግለሰቦች ላይ ሁሉ ተፈጻሚነት አለው ማለት ነው፡፡ ቅንጅት በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሚደገፍ ዐቃቤ ሕጉ በ75 ሚሊዮን ሕዝባችን ላይ ክስ አለማቅረቡ በመዘንጋት ይሆን? ይህንን ተከትሎ ነው ዐቃቤ ሕጉ በተከሳሾች በአንዳችን ላይ የቀረበ በሁሉም ተከሳሾች እንደቀረበ እንዲቆጠርለት የጠየቀው?

ወደ እኛ ሕግ ስንመጣ ከዚህም የበለጠ ኢፍትሃዊነት ይገጥመናል፡፡ በመጀመሪያ ቅንጅት ወንጀለኛ ድርጅት(criminal organization) ነው የሚል ሕግ የለም፡፡ በተጨማሪም የአንድ ድርጅት ዓላማን የሚደግፍ ሰው የድርጅቱ መሪዎች ሠርተውታል በተባለ ወንጀል አባሪነቱ(consfire) ማድረጉ ሳይረጋገጥ በወንጀል ሊጠየቅ ይችላል የሚል ሕግ የለም፡፡ ስለሆነም ዐቃቤ ሕጉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ የሌሉ ድንጋጌዎችን ለመፍጠር ይዳዳዋል፡፡ ይህ አካሄድ "ሕግ ከሌለ ወንጀል የለም" ወይንም(no crime without prior low) ወይንም በተሻለ አገላለጽ(nullum Crimean sine lege) የሚለው ዓለም ሁሉ የተቀበለውና ዓለም ሁሉ የሚሠራበት ኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግም የተጠቀሰ መርህ ወይንም ዶክትሪን ይጥሳል፡፡

በክቡራን ዳኞች ፊት የተጋረጠው አላፊነት ቀላል አይደለም አንድ ወታደር ጥፋት ቢያጠፋ በበላይ መኮንን ታዝዤ ነው ይል ይሆናል አንድ የመንግስት ሠራተኛ ቢያጠፋ አለቃዬ አዞኝ ነው ሊል ይችል ይሆናል ዳኛ ለማንም ተጠያቂ ስለሆነ ለሚፈርደው ፍርድ ለሚያስከትለው ሃላፊነትና ውጤት ተጠያቂ ሙሉ በሙሉ እራሱ ብቻ ነው ፡፡

ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣል እንዲሉ ዳኛ ቢያጠፋ በምን ይዳኛል፡፡ ዳኛ ቢያጠፋ በታሪክ፣ በሕሊናው፣ በልጆቹና በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይዳኛል፡፡

የአገራችን ሕዝብ ለሕግ ከበሬታ ወይንም ንቀት ይኖረው እንደሆን በዚህ ክስና ፍርድ ይወሰናል፡፡ አንድ ሠው በአልሠራው ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል ተብሎ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የተፈረደበት እለት ፍትሕ ሞቶአልና መርዶ መቀመጥ. ሙሾ ማውረድ ይገባናል፡፡ ሕዝባችን በፍርድ ቤት ያለው እምነት ይሟጠጣል የኑረምበርግ ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ ሮበርት ጃክሰን ፍ/ቤቱ ነፃና ገለልተኛ መሆን እንደሚገባው ሲያሳስቡ "ዓለም በተከሳሾች ብቻ ሊፈርድ ለተቋቋመው ፍ/ቤት ክበሬታ የለውም፡፡" (the world yield no respect to courts that are merely organized to convinent) ሮበርት ጃክሰን ብለው ነበር፡፡

## “ለአገራችን ጥቅም መቆም ብቻ ከሆነ በእኛና በኢሕአዴግ መካከል ያለዉ ልዩነት ትንሽና በቀላሉ ሊፈታ የሚችል ነዉ !

*ዶር ያዕቆብ ሃይለማሪያም*



### ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ

አገራችን በብዙ ፓለቲካዊ ኢኮኖሚአዊና ማህበራዊ ችግሮች ተተብትባለች። በእንገታችን ዙሪያ የተጠመጠሙ ማነቆዎች እየጠበቁ እየሄዱ ነው። ድንገትም ሳናውቀው ጉሮሮአችንን አንቀው እስትንፋሳችንን ሊቆርጡት ይችላሉ። አገራችን ለገጠማት መጠነ ሰፊ ችግሮች መፍትሔው ተደጋግሞ እንደተባለው ውይይት ነው። መላው ዓላማችንን ለአገራችን ጥቅም መቆም ብቻ ከሆነ በእኛና በኢሕአዴግ መሀከል ያለው ልዩነት ትንሽና በቀላሉ ሊፈታ የሚችል ነው።
በመጨረሻም መከፋፈላችን የሁላችንም ጥፋት እንደሚያስከትል ተገንዝበን የአለንበት አካባቢ አደገኛነትን ተረድተን በአገር ጉዳይ አሸናፊና ተሸናፊ እንደሌለ አውቀን በወንድማማችነት በእህትማማችነት ስሜት ወደፊት እንቀጥላለን ወይንም የሁላችንም ውድቀት እናፋጥናለን።

የእኛ ጭንቀት ይፈረድብን ይሆን ወይ? ለረጅም ጊዜ እንታሠር ይሆን ወይ? ወይንም በሞት እንቀጣ ይሆን ወይ? አይደለም ጭንቀታችን በእኛ ላይ ቢፈረድ በአገራችን ላይ ሠላምና ዲሞክራሲያዊ ሂደት በፍትሕ ክቡርነት ሊደርስ የሚችለው አደጋ ነው። እኛ እንደሆንን ፊደል ካስትሮ ከ50 ዓመት በፊት በተመሳሳይ የፈጠራ ወንጀል ተከስሰው 8 ሰዓት በፈጀው የክርክር መዝጊያ ንግግራቸው እንዳሉት ″ታሪክ ነፃ ያወጣናል″ (history will absolve me) ። ብለው ነበር ክቡራን ዳኞችም በዚህ ጉዳይ በሰጡት ፍርድም ታሪክ ሲያስታውሰው ይኖራል። ለመጪው ዘመናትም ቀጣዩ ትውልድ የሕግ ተማሪዎችም ምናልባትም ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ይህንን (case) ጉዳይ በሚመረምሩበት ጊዜ ወይ ይኮሩበታል ወይንም ያፍሩበታል የትኛውን እንደሚመርጡ ውሳኔው የክቡራን ዳኞች ይሆናል።

በመጨረሻም በበኩላችን ምንም ወንጀል እንዳልሠራን በጽኑ የምናምን ቢሆንም ወንጀል ሠርተናል ከተባለም ወንጀል ለመሥራታችን በእውነተኛ ማስረጃ ተረጋግጦብን ለሕግ ብቻ ተገዢ በሆነ ነፃና ገለልተኛ ፍ/ቤት ቢፈረድብን ውሳኔው ለመቀበል ወኔው አይገደንም ፣ ማንም ከሕግ በላይ አይደለምና አገራኝ በዲሞክራሲ በነፃነትና በልማት አብባ ለዘላለም ትኑር።